# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የመንግስት ልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ማውጫ ..... i

ቢጋር (Executive summary):- ..... I

ክፍል አንድ ..... 1

መግቢያ ..... 1

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ተልዕኮ፣ ሥልጣንና ተግባር ..... 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሠው ኃይል ..... 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ..... 4

የኦዲቱ ዓላማ ..... 5

የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ..... 5

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ..... 5

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ..... 6

የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process Description) ..... 7

ክፍል ሁለት ..... 8

ግኝቶች ..... 8

በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ:- ..... 8

የመንግስት የልማት ድርጅቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ዕቅድ የሚያዘጋጁ መሆኑን በተመለከተ:- ..... 10

የነዳጅ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓትን በተመለከተ:- ..... 11

የየልማት ድርጅቶቹ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች የኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ ጌጅ ያላቸው መሆኑን በተመለከተ: ..... 12

የነዳጅ ዲፖ ያላቸው የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ፡-.......... 14

በልማት ድርጅቶች ወጥ የሆነ የተሽከርካሪና የማሽነሪዎች ታሪክ ማህደር እና የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤ .......... 15

በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትን በተመለከተ፡- .......... 17

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ትንተና እና ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ፡-.......... 19

የልማት ድርጅቶቹ ነዳጅ አጠቃቀም ላይ በሚከሰቱ ግድፈቶችና ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፡- .......... 20

የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ላይ ስልጠና መሰጠቱን በተመለከተ፡- .......... 23

ክፍል ሦስት .......... 24

መደምደሚያ .......... 24

የማሻሻያ ሃሳቦች .......... 27

አባሪ 1. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር .......... 30

አባሪ 2. የኦዲት መመዘኛ መስፈርት .......... 31

አባሪ 4፡ በወር ውስጥ ከተፈቀደው የነዳጅ ኮታ (200 ሊትር) በላይ የተቀዳ ነዳጅ .......... 37

## ቢ.ጋር (Executive summary):-

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2009 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ መንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ላይ የተከናወነ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የሶስት በጀት ዓመታትን ከ2006- 2008 ዓ.ም እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን በማከተት ነው፡፡

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚ/ር በአዋጅ 916/2008 ሲቋቋም የልማት ድርጅቶችን የኮርፖሬት አስተዳደርና የፋይናንስ አፈፃፀማቸውን ሊከታተልና ሊደግፍ፣ መንግሥት ከነደፋቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እንዲሁም የኢኮኖሚ ግቦች አንፃር የተቃኘ ስትራቴጂያዊና ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ሊያደርግ፣ ሊያጸድቅና አፈፃፀማቸውንም ሊከታተል እንዲሁም በኢኮኖሚ ውስጥ ተገቢ ድርሻቸውን መወጣት የሚያስችላቸውን ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደር አሰራር በመዘርጋት፣ ለግብ ስኬታቸውም መሠረታዊ አቅጣጫዎችን በመንደፍና ስራ ላይ እንዲውሉም ሊያደርግ እንደሚገባ ተጠቅሷል፡፡

የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ላይ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን አያያዝ፣ ስምሪት እና አጠቃቀም የሚወስን መመሪያ እንዲሁም ከመንግስት ተሽከርካሪዎች ምዝገባ፣ አያያዝ፣ ስምሪት እና አጠቃቀም ጋር በተገናኘ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸው ቅጾች የተዘጋጁ በመሆኑ እነዚህ ቅፆች የመንግስት ልማት ድርጅቶችም እንዲጠቀሙባቸው በሚል የአሰራር ሥርዓት የተቀመጠ ቢሆንም የመንግስት የልማት ድርጅቶችም ከራሳቸው ባህሪ ጋር በማጣጣም ባለመተግበራቸው የሚከተሉት ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

- የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ዕቅድ ሲታቀድ የተሽከርካሪዎቹንና ማሽነሪዎችን ብዛት፤ ዓይነትና የነዳጅ ፍጆታን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ እና መካተት ያለባቸው መነሻዎችን ሳያገናዝብ በጥቅል የሚታቀድ መሆኑ፣
- የልማት ድርጅቶች ሚ/ር ወጥ /Standardized/ና ወቅታዊ የሆነ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፤ የነዳጅ አጠቃቀም፤ የቁጥጥር እና አስተዳደርን አስመልክቶ በመንግስት የወጣውን መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ያላደረገ፣ ከልማት ድርጅቶቹ ባህሪ ጋር

በማጣጣም መመሪያ ያላዘጋጀና የልማት ድርጅቶቹ እራሳቸው እንዲዘጋጁና ስራ ላይ እንዲያውሉ ያልተደረገ እና ጥናትም ያልተካሄደ መሆኑ፣

- በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ዲፖ አስተዳደር የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋና መመሪያ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- የልማት ድርጅቶቹ ወጥ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ የነዳጅ፣ የዘይት እና የቅባት መመዝገቢያ ቅጽ እና የግል ማህደር (ሎግ ቡክ) አዘጋጅተው ተግባራዊ ያላደረጉ መሆኑ፣
- የእያንዳንዱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን ተመዝግቦ የማይታወቅና ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ የነዳጅ ጥያቄ ማቅረብ ያለባቸው የተሞላው ነዳጅ ምን ያህል ሲቀረው መሆን እንዳለበት የሚገለጽ መስፈርት /Standard/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- እያንዳንዱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ መስፈርት ያልወጣላቸው መሆኑ፣
- የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ፍጆታ ኮታ ያልወጣላቸው መሆኑ፣
- የልማት ድርጅቶቹ እያንዳድንዱ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች የሚጠቀምበትን ነዳጅና የሚጓዝበትን ኪሎ ሜትር ከአምራች ኩባንያው በሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የማይነጻጸር መሆኑ፤
- የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ኪሎ ሜትር ቆጣሪው/ ጌጅ የሚሠራ ስለመሆኑ በየጊዜው የማይረጋገጥ እና ጌጃቸው ለማይሠሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋና በዛም መሠረት ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ያልተዘረጋና በዚሁ መሠረት የግብረ መልስ አሰጣጥ ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ሥራ ላይ ሳይሆኑ ሥራ እንደሰሩ እየተደረገ ነዳጅ የሚቀዳ መሆኑ፣
- የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የስምሪት ባለሙያዎች የስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አለመከናወናቸው፣

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ ሊሆን የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ሚ/ር መ/ቤቱ በማዘጋጀት የቁጥጥር፣ የክትትልና የግብረ መልስ ሥርዓት ሊዘረጋ እና አስፈላጊውን ግብረ መልስ በወቅቱ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ዕቅድ የተሽከርካሪዎቹንና ማሽነሪዎችን ብዛት፤ ዓይነትና የነዳጅ ፍጆታን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡
- በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ዲፖ አስተዳደር የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- እያንዳንዱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ መስፈርት ሊወጣላቸው እና በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ፍጆታ ኮታ /በሰዓት/ ሊወሰንላቸው እና በዚሁ መሰረት ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፡፡
- ጌጃቸው ለማይሠሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
- በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር ሪፖርት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡
- የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የስምሪት ባለሙያዎች የስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡

## ክፍል አንድ

### መግቢያ

1. መንግስት በኢኮኖሚ ዘርፍ ያለውን ሚናና ተሳትፎ በመለወጥና የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ድርሻ በማስፋፋት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን አስፈሊጊ በመሆኑ የልማት ድርጅቶች በመንግስት ይዞታ ስር እስካለ ድረስ ተወዳዳሪና አትራፊ ሆነው በመቀጠል የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በማስፈፀምና ኢኮኖሚያዊ እድገት በማምጣት ረገድ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ የሚያስችል አመራርና ድጋፍ መስጠት አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈጸም የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን በማዋሃድ ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በመባል በአዋጅ ቁጥር 412/1996 የተቋቋመ ሲሆን ኤጀንሲው በሥሩ የሚተዳደሩ የልማት ድርጅቶችን በውጤት ለመምራት፣ የልማት ድርጅቶች የገበያና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግና በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥና በመሳሰሉት መንገዶች አቅማቸውን በመገንባት ዘመናዊ የኮርፖሬት አመራር ሥርዓት ፕሮግራሞችን በመተግበር ውጤታማነታቸው እንዲሻሻል ለማድረግ እየሰራ የነበረ ሲሆን ፡፡

2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ የማሰለፍ ራዕይ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ሆነው ይህንኑ ሀገራዊ ራዕይ ዕውን ለማድረግ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 መሠረት ተቋቁሟል፡፡

3. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቀደም ሲል የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ይባል ለነበረው መስሪያ ቤትና ለተለያዩ የመንግስት አካላት ተጠሪ የሆኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ያሏቸውን ድክመቶችና ጥንካሬዎች በማጥናትና የተለያዩ አገሮችን ተሞክሮዎች በመዳሰስ በተገኘው ውጤት መሠረት ለልማት ድርጅቶቹ የተቀናጀ ስትራቴጂያዊ አመራር

ለመስጠት፣ የመልካም አስተዳደር አቅማቸውን ለማጎልበት፣ የማስፈፀም አቅም ውስንነታቸውን ለመቅረፍ፣ የማኔጅመንት፣ የአመለካከት፣ የተነሳሽነት፣ ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ ወዘተ ችግሮቻቸውን ለመፍታትና ድርጅቶቹን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የማድረግ ዓላማዎችን ይዞ የተቋቋመ ሲሆን የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራምንም ጎን ለጎን ያከናውናል፡፡

## የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ተልዕኮ፤ ሥልጣንና ተግባር

### ተልዕኮ

4. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ግልፅ አሰራር ይዘውና የኮርፖሬት አመራርና የፋይናንስ ሥርዓት ዘርግተው እንዲሁም የቴክኖሎጂ አቅም ፈጥረው ውጤታማና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማስቻል የአገሪቱን ኢኮኖሚ መደገፍ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተልዕኮ ነው፡፡

### ሥልጣንና ተግባራት

5. ለሚኒስቴሩ በአዋጁ የተሰጡት ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት፡-

ተጠሪነታቸው ለሌላ ተቆጣጣሪ አካል የሆኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን፡-

☞ የኮርፖሬት አስተዳደርና የፋይናንስ አፈፃፀማቸውን መከታተልና መደገፍ፡፡

☞ መንግሥት ከነደፋቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እንዲሁም የኢኮኖሚ ግቦች አንፃር የተቃኘ ስትራቴጂያዊና ዓመታዊ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣ ማፅደቅና አፈፃፀማቸውንም መከታተል፤

☞ በኢኮኖሚ ውስጥ ተገቢ ድርሻቸውን መወጣት የሚያስችላቸውን ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደር አሰራር መዘርጋት፣ ለግብ ስኬታቸውም መሠረታዊ አቅጣጫዎችን መንደፍና ስራ ላይ እንዲውሉም ማድረግ፤

☞ የትርፍ ድርሻ ክፍያ ፖሊሲ ከሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ጋር መንደፍና ስራ ላይ እንዲውልም ማድረግ፤

☞ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያላቸውን ተወዳዳሪነት ከጊዜ ወደጊዜ እንዲያሻሽሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ የመረጃ ድጋፍ መስጠትና በገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚወጣው መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ ላይ በመመስረት

የልማት ድርጅቶች ቦንድ የሚያወጡበትንና የሚገዙበትን እንዲሁም ከውጭና ከአገር ውስጥ ብድር የሚወስዱበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

- ግልፅ የአሰራር ሥርዓት እንዲከተሉ ማገዝና ወቅታቸውን የጠበቁ ትክክለኛ የፋይናንስና የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች የሚያቀርቡበትን ሥርዓት መዘርጋት፤
- የፋይናንስ አጠቃቀምና የብድር ሁኔታዎችን በቅርብ መከታተልና ስለፋይናንስ አፈፃፀማቸውም ተገቢውን ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ማሰራጨት፤
- ካፒታል ለማሳደግ የሚያቀርቡትን ጥያቄ መመርመር፣ ለመንግስት የውሳኔ ሃሳብ አቅርቦ ማስወሰንና አፈፃፀሙንም በቅርብ መከታተል፤
- የቦርድ አባላትን መመደብ፣ ማንሳት፣ ሊከፈላቸው የሚገባውንም አበል መወሰን፣ የቦርድ አሰያየምና አነሳስ መመሪያዎችን ማዘጋጀትና የልማት ድርጅቶች ሙያው፣ ክህሎቱና መልካም ስብዕና ባላቸው ኃላፊዎች የሚመሩበትን ስርዓት መዘርጋት፤
- እንዲፈርሱ፣ ከሌላ ድርጅት ጋር እንዲዋሃዱ ወይም እንዲከፋፈሉ ወይም እንዲሸጡ ለመንግሥት የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብና ይህንን በተመለከተ ግልፅ መመሪያ ማዘጋጀት፤
- ለትርፍ ብቻ የማይሰሩ ሲሆንና እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- ለምርምርና ለፈጠራ በቂ በጀት እንዲመድቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና የተገኘውንም የምርምር ውጤት እንዲስፋፉ ማድረግ፤
- የሚማማሩበትን መድረክ አዘጋጅቶ ልምድ እንዲለዋወጡ ማድረግና ራሱም የድርጅቶቹን አቅም የሚያሳድጉ የተለያዩ ስልጠናዎችን አዘጋጅቶ መስጠት፤
- ለኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን እያጠና በመንግስት ልማት ድርጅትነት እንዲቋቋሙ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ስራ ላይ ማዋል፣ እንዲሁም መስፋፋት የሚኖርባቸውን ነባር የልማት ድርጅቶች በጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲስፋፉ ማድረግ፣
- በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውስጥ መንግሥት ያለውን የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሠው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር ፤

6. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሠረት የተቋቋመ ሲሆን አንድ ሚኒስትር፣ አራት በሚ/ር ዴኤታ የሚመሩ ዘርፎች (የማኑክቸሪንግ ኢንዱስትሪና ግብርና ዘርፍ፣ የትራንስፖርትና ኮሚኒኬሽን ዘርፍ፣ የማዕድን፣ ኢነርጂና ኮንስትራክሽን ዘርፍ እና ኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታዎች) ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ዘርፎች በሥራቸው ሁለት ሁለት ዳይሬክቶሬቶች ሲኖራቸው ለሚኒስትሩ ቀጥታ ተጠሪ የሆኑ ስድስት ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም በሥሩ ስድስት ዳይሬክተሮችን የያዘ የሚኒስትር ጽ/ቤትን በመያዝ የተዋቀረ ነው፡፡ በአጠቃላይ አንድ ሚኒስትር፣ አራት ሚ/ር ዴኤታዎች፣ 20 ዳይሬክቶሬቶች እና አንድ የሚ/ር ጽ/ቤትን በአደረጃጀቱ በመያዝ ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር **በአባሪ 1** ተያይዞዋል፡፡

### የሰው ኃይል

7. የሰው ኃይል ፍላጎትን በተመለከተ ሚኒስቴር መ/ቤት አዲስ በመሆኑ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት አደረጃጀቱንና የሰው ኃይል ፍላጎቱን አጥንቶ ለመንግሥት አቅርቦ ባፀደቀው መዋቅር መሠረት ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት ቀን ድረስ 336 የሰው ኃይል እንዲኖረው የተፈቀደ ሲሆን፡፡ በ2008 ዓ.ም 215 ሠራተኞች ሲኖሩት ወንድ 115 ሴት 100 እንደሆነ ከተከለሰ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

8. የሚኒስቴር መ/ቤት የገቢ ምንጭ ከመንግሥት የሚመደበው በጀት ብቻ ሲሆን የገቢና የወጪ መግለጫው በሰንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | ገቢና ወጪ | 2006 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | 2008 ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የተመደበለት በጀት | 24,013,410 | 27,713,517 | 47,888,325 |
| 2. | የበጀት አጠቃቀም ወጪ | 20,325,931 | 24,833,820 | 46,993,015 |
| | አጠቃቀም በመቶኛ | 84.64% | 89.61% | 98.13% |

## የኦዲቱ ዓላማ

9. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት መዘርጋቱንና ለነዳጅ የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ ችግሮችን በመለየት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድባቸው በማድረግ የአሰራር ግድፈቶችን ለማስተካከል የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለመስጠት ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

10. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ **"በመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የመንግስት ልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር በቁጠባ፤ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን መገምገም"** የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

### የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ

11. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሥር ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተመርጠዋል፡፡ እነሱም:-

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማደረጋቸውን እንዲሁም በጥናት ላይ የተመሰረተ የነዳጅ ፍላጎት ዕቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት እየተገበሩ መሆኑን መገምገም፣
- በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተተገበረ መሆኑን ማጣራት የሚሉ ናቸው፡፡

#### የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

12. ከላይ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ ሠላሳ ሶስት (33) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የስቶክ ማኔጀመንት መመሪያ፣ የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ፣ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የተካሄደ ጥናት ሪፖርት፣ የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና ቁጥጥር መመሪያ፣ የመንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅት ተሽከርካሪዎች ግዥ ሥምሪት አጠቃቀምና ጥገና መምሪያ፣ የመኪና አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ እና የመልካም ተሞክሮዎች ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የልማት ድርጅቶቹ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ቀርቦላቸው ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) **በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡**

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

#### የኦዲቱ ወሰን

**13.** ዝርዝር ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2006 የበጀት ዓመት እስከ 2008 በጀት ዓመት ድረስ ያለውን ሲሆን ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚቆጣጠራቸው በናሙና በተመረጡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ ነው፡፡

#### የኦዲቱ ዘዴ

14. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የልማት ድርጅት ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር መጠይቅ በማድረግ፣ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስ ሲሆን በተጨማሪም ኦዲቱ በናሙና በተመረጡ በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ስር (የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር እና የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት)፤ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ስር (የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ ዋና መ/ቤት እና ሻሸመኔ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፣ የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን አዲስ አበባ)፤ አሰላ ብቅል ፋብሪካ እና ሐዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት በአካል በመገኘት መጠይቅ በማድረግና የተለያዩ

መረጃዎችን በመከለስ በተሰበሰቡት ማስረጃዎች ላይም አስፈላጊውን ትንተናና ንፅፅር (Analysis) በማካሄድ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የአሰራር ስርዓት መግለጫ (Process Description)

15. የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ማለት የንብረት አጠቃቀም እና አወጋገድ ላይ የመተግበር እና ውሳኔ የመስጠት ሂደት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሠረት የመንግሥት ንብረት ማለት ከመንግስት ገንዘብ እና መሬት በስተቀር የፌዴራላዊ መንግሥት ሐብት የሆነ ማናቸውም ንብረት ነው፡፡ ይህ የመመሪያ ትርጓሜ በመንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ ላይ ብቻ ሳይሆን በትውስት ወይም በሌላ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቶች የጥበቃ ኃላፊነት ሥር ለሚገኙት ንብረቶች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በዚህ መመሪያ ተሽከርካሪ እና ነዳጅ ከስቶክ እንደሚመደቡ ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግስት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 ላይ የመንግስት ተሽከርካሪዎችን አያያዝ፣ ስምሪት እና አጠቃቀምን የሚወስን መመሪያ እንዲሁም ከመንግስት ተሽከርካሪዎች ምዝገባ፣ አያያዝ፣ ስምሪት እና አጠቃቀም ጋር በተገናኘ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸው ቅጾች የተዘጋጁ በመሆኑ እነዚህ ቅፆች የመንግስት ልማት ድርጅቶችም እንዲጠቀሙባቸው በሚል የአሰራር ሥርዓት ዘርግቷል፡፡ የአሰራር ሥርዓቱ (Process Description) ስዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 3** ይመልከቱ፡፡

## ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

***በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ መዘጋጀቱን በተመለከተ:-***

16. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የልማት ድርጅቶች የሚጠቀሙበት ወጥ የሆነ /Standardized/ በበቂ ጥናት ላይ የተመሰረተ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ የቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያን ሊያዘጋጅና በስሩ ላሉ ልማት ድርጅቶች ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ የተዘጋጀውም መመሪያ ከየወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም እየተጠና ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

17. የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በስሩ ያሉ የልማት ድርጅቶች የሚመሩበት ወጥ የሆነ /Standardized/ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ ቁጥጥር እና የአስተዳደር መመሪያን ያላዘጋጀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

18. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የመንግስት ልማት ድርጅቶች:-

- በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን
  - የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር ወጥ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን አስመልክቶ የወጣ መመሪያ የሌለ መሆኑ፣
  - የቀድሞ የእርሻ መሳሪያዎችና የቴክኒክ አገልግሎት አ.ማ ለመስክና አነስተኛ ተሽከርካሪ መኪኖች በቀን 13 ሊትር እንዲቀዱ በሚል ደብዳቤን በቀን 16 ኀዳር 1997 በደብዳቤ ቁጥር 06/123/57 መነሻ በማድረግ የሚጠቀሙ መሆኑ፣
  - የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የነዳጅ አጠቃቀም፣ ቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያ የሌለው መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን
  - የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ የነዳጅና ቅባቶች አጠቃቀምና ቁጥጥር መመሪያ ህዳር/2008 ዓ.ም የተዘጋጀ ቢኖርም መመሪያው በተግባር ላይ ያልዋለ መሆኑን፣

- የቀድሞው የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅቱ በ1999 ዓ.ም የወጣ መመሪያ ቢኖርም መመሪያው ተግባራዊ ያልተደረገ እና መመሪያው ከተዘጋጀ በኋላ ወቅታዊ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፣
- አሰላ ብቅል ፋብሪካ፣ ኮስቲክ ሶዳ አክሲዮን ማህበር፣ የፍል ውሃ አስተዳደር እና የግዮን ሆቴሎች ድርጅት የራሳቸው የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ የቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያ የሌላቸው መሆኑን፣
- የአርስቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ የቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያ አዘጋጅቶ እየሰራበት መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

19. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የየልማት ድርጅቶቹ ኃላፊዎች በቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ነዳጅና ቅባት በንብረት የሚታወቅ በመሆኑ በአጠቃላይ የንብረት አስተዳደር መመሪያ ውስጥ የተካተተ እንጂ ራሱን የቻለ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፤ የነዳጅ አጠቃቀም፤ የቁጥጥርና አስተዳደር አስመልክቶ መመሪያ አለመኖሩን አስረድተዋል፡፡

20. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ሁሉም ድርጅቶች የተለያዩ የኢንዱስትሪ ባህሪ ያላቸው ስለሆነ ወጥ መመሪያ ማዘጋጀት ባይጠበቅባቸውም ሚ/ር መ/ቤቱ ለሁሉም ድርጅቶች የሚሰራ ወጥ የኮርፖሬት ፋይናንስና አስተዳደር የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ሲውል የሚስተካከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ወጥ መመሪያ ለማዘጋጀት ያስቸግራል ቢሉም ሁሉም የሚጠቀሙት በአብዛኛው ተመሳሳይ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

21. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ለሚቆጣጠራቸው የልማት ድርጅቶች ወጥ /Standardized/ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፤ የነዳጅ አጠቃቀም፤ የቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያ ያላዘጋጀና እንዲሁም የልማት ድርጅቶቹ እራሳቸው እንዲዘጋጁና ስራ ላይ እንዲያውሉ ያልተደረገ እና ጥናቱም ያልተካሄደ በመሆኑ ለአሠራርና ለቁጥጥር አመቺ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም ስርዓት እንዳይኖርና

ሥርዓቱ በሌለበት ለነዳጅ የወጣው ገንዘብ ትክክለኛ ሥራ ላይ ውሏል ለማለት ያዳግታል፡፡

**የመንግስት የልማት ድርጅቶች በጥናት ላይ የተመሰረተ የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ዕቅድ የሚያዘጋጁ መሆኑን በተመለከተ፡-**

22. ሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለተሽከርካሪዎቹ የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር በጥናት ላይ በመመስረት ዕቅድ ሊያዘጋጁ እና ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የሚዘጋጀውም ዕቅድ ያሏቸውን ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና ማሽነሪዎች ብዛት፣ አይነት እና ያላቸውን የቴክኒክ ብቃት ከግምት ውስጥ በማስገባት ኢኮኖሚያዊና ብቃት ያለው አጠቃቀም እንዲኖር የሚያደርግ ሊሆን ይገባል፡፡

23. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር፤ የተፈጥሮ ሙጫና የደን ውጤቶች ምርትና ገበያ እና አርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ የፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት፤ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በየዓመቱ የነዳጅና የቅባት ፍጆታ ዕቅድ የሚያዘጋጁ ቢሆንም የሚያዘጋጁት ዕቅድ በጥናት ላይ ያልተመሰረተ (የተሽከርካሪዎቹንና ማሽነሪዎችን ብዛት፤ ዓይነትና የቴክኒክ ብቃት ከግምት ያላስገባ) እና ኢኮኖሚያዊና ብቃት ያለው አጠቃቀም እንዲኖር የሚያደርግ አለመሆኑ ታውቋል፡፡ ከ2006 - 2008 ዓ.ም የነዳጅና የቅባት ፍጆታ ወጪ ከተያዘው በጀት ጋር ሲነጻጸር አፈጻጸሙ ልዩነት እንዳለው እና የማይጣጣም መሆኑን ከየድርጅቶቹ ከነዳጅና ቅባት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለማሳያነት ያህል የአምስት የልማት ድርጅቶችን የሁለት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ዝርዝር እንደሚከተለው በሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

<u>ሠንጠረዥ 1.የልማት ድርጅቶቹን የነዳጅና የቅባት ዕቅድ አፈጻጸምን ዝርዝር መግለጫ</u>

| የነዳጅና የቅባት ዕቅድ አፈጻጸምን (በብር) | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የልማት ድርጅቶቹ ስም | 2007 ዓ.ም | | | 2008 ዓ.ም | | |
| | | ዕቅድ | ክንውን | % | ዕቅድ | ክንውን | % |
| 1. | የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር | 1,434,850 | 2,120,740 | **1.48** | 1,995,300 | 2,028,153 | **1.02** |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2. | በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | 274,356 | 161,605 | **0.59** | 102,878 | 296,190 | **2.88** |
| 3. | የቀድሞው የተፈጥሮ ሙጫና የደን ውጤቶች ምርትና ገበያ | 2,750,000 | 2,692,330 | **0.98** | 2,000,000 | 230,640 | **1.15** |
| 4. | የፍል ውሃ አገልግሎት ድርጅት | 759,000 | 565,500 | **0.75** | 617,000 | 708,500 | **1.15** |
| 5. | የቀድሞው የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት | 515,548,327 | 131,127,694 | **0.25** | 318,044,376 | 179,176,822 | **0.44** |

24. ስለጉዳዩ የልማት ድርጅቶቹ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የነዳጅ ፍጆታ እንዲጨመር ካደረጉት ዋነኛ ምክንያት አንዳንድ ማሽነሪች (ለምሳሌ ሞዴላቸው 1221 የሆኑት ቤለሩስ ትራክተሮች) የጥራት ችግር ያለባቸው በመሆኑ ዘይት የሚያፈሱ ስለሆነ ከተገመተው በላይ የዘይት ፍጆታቸው መጨመሩን፣ የነዳጅ ፍጆታ ዕቅድ ሲታቀድ የድርጅቶቹን ገቢ 35 በመቶ ለነዳጅ ይውላል በሚል የሚታቀድ እንጂ የተሽከርካሪዎቹንና ማሽነሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ታሳቢ በማድረግ የማይታቀድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

25. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ በዝርዝር የቀረቡት ድርጅቶች የራሳቸው የሆነ አደረጃጀት ያላቸው እና በአዋጅ ቁጥር 25/84 የሚተዳደሩ ስለሆነ ዕቅዳቸው የሚጸድቀው በስራ አመራር ቦርድ በመሆኑ የታየው ልዩነት በዓመቱ መጨረሻ በተጠየቀው የበጀት ጭማሪ ምክንያት መሆኑን መረዳታቸውን እንዲሁም ለወደፊቱ ድርጅቶቹ ያለባቸውን የአሰራር ክፍተት በመለየት ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

26. የነዳጅና የቅባት ዕቅዱ ሲታቀድ በተገቢ ጥናት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ ለልማት ድርጅቶቹ የሚመደበው የነዳጅ በጀት እንዲባክንና የመንግስት ልማት ድርጅቶቹ የሚጠበቅባቸውን ውጤት እንዳያስመዘግቡ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽኖ ይፈጥራል፡፡

**የነዳጅ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓትን በተመለከተ፡-**

27. የእያንዳንዱ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ያላቸው የነዳጅ መያዣ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን አስቀድሞ በማወቅ ተመዝግቦ

ሊያዝ ይገባል፡፡ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች በሊትር/ በሰዓት ምን ያህል ነዳጅ እንደሚጠቀሙ መስፈርት /Standard/ ሊወጣ እና የተጨማሪ የነዳጅ ጥያቄ በመስፈርቱ መሰረት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

28. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ከአሰላ ብቅል ፋብሪካ እና ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ከዋና እና ከቃሊቲ ቅ/መ/ቤት ወደ መስክ ስራ የሚላኩ ተሽከርካሪዎች በስተቀር ሁሉም የልማት ድርጅቶች ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን የማይታወቅና ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ፣ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ነዳጅ መቅዳት የሚችሉት ምን ያህል ሊትር ነዳጅ በሰልባቶዮ/በታንከራቸው ውስጥ ሲቀራቸው እንደሆነ የተቀመጠ መስፈረት /Standard/ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

29. በናሙና ተመርጠው በታዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የነዳጅ ታንከር (ሰልባትዮ) የሚይዘው መጠን በትክክል ተመዝግቦ ያልተያዘ በመሆኑ ለወደፊቱ የሚያስተካክሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

30. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ተጠይቀው ለወደፊቱ ከየድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድና ማኔጅመንት አባላት ጋር በመነጋገር የሚፈታና የሚስተካከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

31. የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የነዳጅ ታንከር (ሰልባትዮ) የሚይዘው መጠን በትክክል ተመዝግቦ አለመያዙና የታንከር መጠናቸው የማይታወቅ መሆንና ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ነዳጅ መቅዳት የሚችሉት ምን ያህል ኪሎሜትር /ሰዓት ካጠናቀቁ በኋላ መሆኑን የሚገልጽ የተቀመጠ መስፈረት /Standard/ አለመኖሩ ነዳጅ ከሚፈለገው መጠን በላይ እንዲቀዳ በር በመክፍት ለብክነት ከመዳረጉም በላይ ለህገወጥ አሰራርና ምዝበራ በር ይከፍታል፡፡

**የየልማት ድርጅቶቹ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች የኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ ጌጅ ያላቸው መሆኑን በተመለከተ፡-**

32. የእያንዳንዱ ተሽከርካሪው፣ ማሽነሪ እና መሳሪያ የነዳጅ ኪሎ ሜትር ቆጣሪው /ጌጅ/ የሚሠራ መሆኑን በየጊዜው መረጋገጥ አለበት፡፡ ጌጃቸው ለማይሠሩ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎች እና መሳሪያዎች ቶሎ ተጠግነው እንዲሰሩ ሊደረግ እና እስኪጠገኑ ድረስ የነዳጅ አጠቃቀማቸውን ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ እና በዚሁ መሠረት ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት

- ሁሉም የልማት ድርጅቶች ምን ያህል ተሽከርካሪዎቻቸው ኪሎ ሜትር ቆጣሪው (ጌጅ) እደሚሠራና እንደማይሠራ የመለየት ስራ እንዳላከናወኑ እንዲሁም
- ጌጃቸው ለማይሰራ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ያልዘረጉና የነዳጅ ጥያቄ በመቅረቡ ብቻ እንዲቀዱ የሚደረግ መሆኑ፣
- በኢትዮጲያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ስር የቀድሞው እርሻና ቴክኒክ አገልግሎት ኢ.ማ እንዲሁም በኢትዮፒያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት በሰረተ ልማት ዘርፍ እና ውሃ ስራዎች ኮርፖሬሽን ለአንዳንድ ተሽከርካሪዎች የቀንም ሆነ ሳምንታዊ ኮታ የተቀመጠላቸው ቢሆንም በጥናት ላይ ያልተመሰረተ እና ኮታውም ከሥራ ሽፋናቸው ጋር ተነጻጽሮ ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

34. ስለጉዳዩ በናሙና ተመርጠው በታዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ጌጅ የሌላቸው ወይም ጌጃቸው የማይሰሩ ተሽከርካሪዎች ባይመዘገቡም በተለምዶ የሚያውቋቸው መሆኑን፣ ጌጃቸው ለማይሰሩ ተሽከርካሪዎች በታንከራቸው ላይ የሽቦ ወንፊት ለማሰራት ዕቅድ መያዙን፣ ጌጃቸውና ኪሎ ሜትራቸውን ለማሰራት መሞከሩን እና ዕቃው በገበያ ላይ ባለመገኘቱ ሊጠገኑ አለመቻላቸውን፣ ጌጃቸው የማይሰሩ ሞዴላቸው የቆዩ ተሽከርካሪዎች ስለሆኑ ቆጣሪ ከገበያ ላይ መጥፋቱን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም በቅድሚያ ጌጃቸው የማይሰሩ ተመዝግበው ተይዘው የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባ ስለነበር የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

35. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው ለወደፊቱ ታይተው እና ተፈትሸው እንዲስተካከል የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

36. ጌጃቸው የማይሠሩ ተሽከርካሪዎች ተለይተው የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱ ለነዳጅ የሚመደበውን በጀት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል በማድረግ ነዳጅ ለብክነት እንዲጋለጥ፣ ተሽከርካሪው በተቀዳለት

ነዳጅ ምን ያህል ኪሎ ሜትር የተጓዘ መሆኑን በማረጋገጥ መደበኛ ጥገና እንዲደረግላቸው ማድረግ የማያስችል ከመሆኑም በላይ ለመንግስት ሀብት እንዲመዘበር በር ይከፍታል፡፡

**የነዳጅ ዲፖ ያላቸው የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ፡-**

37. የነዳጅ ዲፖ ያላቸው ድርጅቶች ነዳጅ ሲገዛም ሆነ ወደ ዲፖ ሲገለበጡ ግልፅ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የነዳጅ ማደያ መሳሪያውም በየአመቱ ካሊቢሬት ሊደረግ ይገባል፡፡

38. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የነዳጅ ማጠራቀሚና ማደያ ዴፖ ያላቸው

- በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
  - የነዳጅ ማደያ ዲፖዎች በ1972 ዓ.ም የተገነቡና ለረጅም ጊዜ እድሳት ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
  - የነዳጅ መቅጃ መሳሪያዎቹ በትክክል አገልግሎት የሚሰጡ ስለመሆኑ (calibration test) በየወቅቱ አለመደረጉን፣
  - የነዳጅ መቅጃ የመጠን መቁጠሪያቸው (counter) የማይሰራ ዴፖዎች መኖራቸውን፣
  - በነዳጅ ማደያ ዲፖዎቹ የእሳት አደጋ መከላከያ (Fire extinguisher) አለመኖሩን፣
- በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ
  - በስሩ ያሉት ዴፖዎች የሚመሩበት የነዳጅ ዲፖ አስተዳደር መመሪያ የሌለው እና የቁጥጥር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣
- በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን
  - ማጠራቀሚያ ታንከሩ በ1998 ዓ.ም የተተከለና ከዛ በኋላ እድሳትና (calibration test) ያልተደረገለት መሆኑን፣
- በአብዛኛዎቹ የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ማደያ ዲፖዎች የነዳጁን ጥራት አረጋግጠው የሚረከቡበት መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም

- ነዳጅ ለብክነት እንዳይጋለጥ ለማድረግ የነዳጅ የማራገፊያ ሰዓት ያልተወሰነላቸው መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና መስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ስለጉዳዩ በናሙና ተመርጠው የታዩ የልማት ድርጅት ኃላፊዎች ተጠይቀው የነዳጅ ማደያ ዲፖዎች የነዳጁን ጥራት አረጋግጠው የሚረከቡበት መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም ነዳጅ ለብክነት እንዳይጋለጥ ለማድረግ የነዳጅ የማራገፊያ ሰዓት ያልተወሰነላቸው መሆኑን እና በተደጋጋሚ መሳሪያዎቹ እንዲጠገኑ የሚመለከታቸውን የጠየቁ ቢሆንም አለመከናወኑን ለወደፊት የሚያስተካክሉ መሆኑን ገልጸዋል።

40. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ተጠይቀው ድርጅቶቹ በቅርብ ጊዜ በኮርፖሬሽን ደረጃ የተቋቋሙ ስለሆነ በቀጣይ ችግሮቻቸው ተለይቶ የመፍትሄ አቅጣጫ የሚቀመጥ መሆኑን ቢገልጹም ድርጅቶቹ አደረጃጀታቸውን ለወጡ እንጂ አዲስ የተቋቋሙ ባለመሆናቸው ሥርዓቱ ቀደም ብሎ ሊዘረጋ ስለሚገባ ምክንያቱን ለመቀበል አልተቻለም፡፡

41. የነዳጅ ዲፖ ያላቸው ድርጅቶች ነዳጅ ሲገዛም ሆነ ወደ ዲፖ ሲገለበጡና ሲቀዱ ግልፅ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ያልተደረገ እና ማጠራቀሚያ ዲፖዎቹም መደበኛ እድሳት የማይደረግላቸው በመሆኑ በውጭ ምንዛሬ ተገዝቶ የሚመጣን ነዳጅ በከፍተኛ ሁኔታ ለብክነት ተጋላጭ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

**በልማት ድርጅቶች ወጥ የሆነ የተሽከርካሪና የማሽነሪዎች ታሪክ ማህደር እና የነዳጅ አጠቃቀም መመዝገቢያ ቅጽ መዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

42. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይት ፣ የቅባት መመዝገቢያ ቅጽ እና የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ካርድ (ሎግ ቡክ) የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ፤ የሰርቪስ ከጥገናና ወጪዎቻቸው ጋር የሚመዘገብበት የተሟላ የግል ማህደር ሊዘጋጅላቸውና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

43. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር እና የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች

ኮንስትራክሽን ድርጅት እንዲሁም ሌሎች በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ሁሉም የልማት ድርጅቶች የነዳጅና ቅባት መጠየቂያ ሰነድና ከስቶር ወጪ ማድረጊያን ብቻ የሚጠቀሙ እንጂ ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ነዳጅ ሲቀዳ የነዳጅ፣ የዘይት እና የቅባት መመዝገቢያ ቅጽ /ሎግ ቡክ/ በማዘጋጀት ተግባራዊ አለማድረጋቸውን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. በተጨማሪም በናሙና ከታዩት ድርጅቶች ውስጥ ከአሰላ ብቅል ፋብሪካ፣ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን እና የኬሚካል ኮርፖሬሽን በስተቀር ሁሉም የልማት ድርጅቶች ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ካርድ በማዘጋጀት የየዕለቱንና የየወቅቱን መረጃዎች ማለትም የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ፣ የሰርቪስ ከጥገናና ወጪዎቻቸው ጋር በመነጻጸር የሚመዘገብበት የግል ማህደር ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

45. የልማት ድርጅቶቹ የበላይ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት መልስ መመዝገቢያ ቅጹ የተዘጋጀ ቢሆንም፣ በአፈጻጸም ላይ በሚታዩ ችግሮችና በሥራ መደራረብ ምክንያት ቅጹን መሙላት ያልቻሉ መሆኑን እና እነዚህን ችግሮች በመከታተል በቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን፣ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ካርድ (ሎግ ቡክ) በማዘጋጀት የየዕለቱንና የየወቅቱን መረጃዎች ማለትም የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ፣ የሰርቪስ ከጥገና ወጪዎቻቸው ጋር የሚመዘገብበት የተሟላ የግል ማህደር አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

46. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የታየውን የአሰራር ክፍተት ለማስተካከል ለወደፊቱ አስፈላጊው ክትትል እና ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

47. እያንዳንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይት እና የቅባት መመዝገቢያ ቅጽን እና ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ካርድ የየዕለቱንና የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ እና ጥገናና ወጪዎቻቸው እና የሚፈለጉ መረጃዎችን በአግባቡ አለመመዝገብ ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት እንዳይኖር በማድረግ የነዳጅ በጀትን በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

**በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትን በተመለከተ፡-**

48. እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል መስፈርት በሚመለከተው አካል ተዘጋጅቶ ጸድቆ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ኮታ ሊቀመጥላቸውና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

49. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ከአሰላ ብቅል ፋብሪካ እና የኬሚካል ኮርፖሬሽን በስተቀር የሁሉም ልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል መስፈርት የሌላቸው መሆኑን፣ ሁሉም በናሙና የታዩ የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዳዲስ ተሽከርካሪዎቻቸው ከአምራች ኩባንያው በሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የማያነፃፅሩና ልዩነቱንም ከምክንያት ጋር የማያስቀምጡ መሆኑ፣ የልማት ድርጅቶቹ ለሚጠቀሙባቸው እያንዳንዱ ጄነሬተር፣ ትራክተር፣ ኮንባይነር እና የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ኮታ (በኪሎ ሜትር ወይም በሰዓት ምን ያህል ነዳጅ ሊጠቀሙ እንደሚችሉ) የሌላቸው መሆኑን እና አገልግሎት የሰጡ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም በየዓመቱ እየተከለሰ ወይም በእርጅና መጠናቸው ወቅታዊ እየተደረገ ተግባራዊ የማይደረግ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለመጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

50. በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ዘርፍ ለእያንዳንዱ ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችል መስፈርት (harmonization rate) ሳይዘጋጅ ነዳጅ ያለገደብ ለአሽከርካሪዎች እንደሚቀዳ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ነገር ግን ድርጅቱ ለአንድ አንድ ተሽከርካሪዎች በወር እንዲጠቀሙ ያስቀመጠውን የ200 ሊትር ናፍጣ ኮታ ጣራ እንኳን ተግባራዊ አላደረገም፡፡ እንደማሳያነት የድርጅቱን የሰኔ ወር 2008 ዓ.ም የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ማስረጃዎች በኦዲቱ ወቅት ሲከለሱ 30 (ሠላሳ) የድርጅቱ ተሽከርካሪዎች በወር ውስጥ መሙላት ካለባቸው በላይ በልዩነት 4,733 ( አራት ሺ ሰባት መቶ ሠላሳ ሦስት) ሊትር ናፍጣ የቀዱ

ሲሆን በተሸከርካሪ ከ20 እስከ 700 ሊትር በብልጫ ተቀድቷል፡፡ ይህም በሰኔ 2008 በነበረው አማካይ የናፍጣ ዋጋ በገንዘብ ሲለወጥ ብር 75,728 የሚሆን በልዩነት ታይቷል፡፡ ይህ የአንዱን ወር በመውሰድ ለማሳያነት የቀረበ ማስረጃ እንጂ ሌሎች ወራት እና ዓመታት ላይ የተቀዳው የነዳጅ መጠን ማስረጃዎቹ በአግባቡ ተጠናቅረው ባለመያዛቸው አስተያየት ለማቅረብ አልተቻለም፡፡ የሰኔ ወር 2008 ዓ.ም ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡- (ዝርዝር ሰንጠረዡን በአባሪ 4 ላይ ተያይዟል፡፡




51. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ተጠይቀው ለወደፊቱ ከየድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድና ማኔጅመንት አባላት ጋር በመነጋገር የሚፈታና የሚስተካከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

52. ድርጅቶቹ ለሚጠቀሙባቸው ለእያንዳንዱ ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች በሰዓት ምን ያህል ነዳጅ እንደሚፈጁ እና ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ አለመታወቁ እና ከአምራች ኩባንያው ከሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር ስለመጣጣሙ የሚረጋገጥበት ስርዓት አለመኖሩ ተሽከርካሪዎች የተጠቀሙት ነዳጅ የተጓዙበትን ኪሎ ሜትር የሸፈነ ስለመሆኑ ለማጣራት እና ነዳጅን በትክክል የተጠቀሙበት መሆኑን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪ

የነዳጅ አጠቃቀም ተገቢው የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት እንዳይኖር በማድረግ የነዳጅ በጀትን በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

**የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ትንተና እና ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ፡-**

53. በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ጭምር በየደረጃው ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

54. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር እና የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ ዋና መ/ቤትና ሻሸመኔ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪና የስራ መሳሪያዎች በሰሌዳ ቁጥር ተለይተው የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት/ሰዓት ጋር በማነጻጸርና በመተንተን በሪፖርት ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

55. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የድርጅቶቹ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ወርሃዊ ሪፖርቱ የሚቀርበው በጥቅል እንጂ እያንዳንዱ ተሽከርካሪና የስራ መሳሪያ በሰሌዳ ቁጥር እየተለየ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸርና በመተንተን እንደማይቀርብ አስረድተው ለወደፊት ከላይ የተገለጹ ሀሳቦች እንዲካተት በማድረግ ሪፖርቱን በዝርዝር እንደሚያዘጋጁ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

56. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ተጠይቀው ለወደፊቱ ጉዳዩን በመፈተሽ የሚያስተካክሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

57. በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የድርጅቶቹ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ በነዳጅ አጠቃቀም ላይ ቁጥጥር እና ክትትል ሥራ ላይ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ የተጠያቂነት ስርዓት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

**የልማት ድርጅቶቹ ነዳጅ አጠቃቀም ላይ በሚከሰቱ ግድፈቶችና ችግሮች ላይ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፡-**

58. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ግድፈቶችና ክስተቶች ሊለዩ ይገባል፡፡ በተከሰቱት ችግሮችና ግድፈቶች ላይም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የቀድሞው የእርሻና ቴክኒክ አገልግሎት አክሲዮን ማህበር እና የአርዳይታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ እና የኢትዮጵያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል፣ ቁጥጥር፣ የግምገማ እና ግብረ መልስ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረት ልማት ዘርፍ የሰኔ ወር 2008 ዓ.ም የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ሪፖርት ላይ፡-

- ተሽከርካሪዎች ነዳጅ በሚሞሉበት ወቅት በተሽከርካሪው የጎን ቁጥር መሰረት እና በአንድ የሂሳብ ቁጥር ብቻ መቅዳት ያለባቸው ቢሆንም 17 (አስራ ሠባት) የሚሆኑት የድርጅቱ ተሽከርካሪዎች በአንድ የጎን ቁጥር እና ከሁለት እስከ ሦስት በሆነ የተለያየ የሂሳብ ቁጥር በሰኔ 2008 ዓ.ም ብቻ በተለያዩ ቀናት 4,942 (አራት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ሁለት) ሊትር ነዳጅ የቀዱ ሲሆን በገንዘብ ሲለወጥ ብር 79,072 (ሠባ ዘጠኝ ሺ ሰባ ሁለት) መሆኑን፣ ከሰኔ ወር 2008 ዓ.ም የነዳጅ አጠቃቀም አፈፃፀም ማስረጃዎች በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ የ2008 ዓ.ም ሰነድ በተከለሰበት ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው በየወሩ ከሚቀርብ ማስረጃ ሪፖርት በአንድ የጎን ቁጥር በተለያየ የሂሳብ ቁጥርና በተለያዩ ቀናት ተሽከርካሪዎቹ ነዳጅ የሚቀዱ መሆኑ በሪፖርቱ እየተገለጸ

ነገር ግን የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ አለመኖሩን ታውቋል፡፡ ዝርዝር ማሳያው እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

| ተ.ቁ | የጎን ቁጥር | የተሰጠው የሂሳብ ቁጥር | የቀዳው ሠራተኛ መለያ ቁጥር (B.NO) | በሰኔ 2008 የተቀዳበት ቀን | የተቀዳ ሊትር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 00003 | 1051; 1141; 1130 | 25860; 31815; 31815 | 13,25,28 | 90 |
| 2 | 00062 | 1273; 1127 | 29688; 24308; 37019 | 3,9,15,22,54 | 214 |
| 3 | 03751 | 1211; 1213 | 22563; 55069 | 3,4,8,17,21 | 235 |
| 4 | 03776 | 1201; 1210 | 10660; 38669 | 2,4,10,14,18,21,24,29, | 273 |
| 5 | 32399 | 1273; 1276 | 27173; 74442; 12927 | 18,21,25 | 68 |
| 6 | 33503 | 1250; 1273 | 25935; | 10,14,21,28 | 900 |
| 7 | 41810 | 1126; 1132 | 92350; 92300; 7366 | 5,14,24, | 110 |
| 8 | 42974 | 1040; 1126 | 45273;211074; 37019 | 4,6,17,27, | 260 |
| 9 | 44961 | 1062; 1060 | 21066 | 3,13,16,17,21,28,40, | 260 |
| 10 | 47490 | 1021; 1126 | 21104;211046 | 7,15,17,20,30 | 340 |
| 11 | 48089 | 1122; 1124; 1144 | 43948 | 2,4,8,14,19,23 | 290 |
| 12 | 50849 | 1130; 1132 | 3186 | 2,6,10,17,20,24,28 | 348 |
| 13 | 55070 | 1051;1052 | 25860 | 2,8,11,15,21,28 | 255 |
| 14 | 55151 | 1273; 1203 | 27186;45591;8368;150 | 2,4,13,19,20,27 | 145 |
| 15 | 56104 | 1144;1143;1141 | 21901;2154;31815 | 3,9,15,20,24,29 | 200 |
| 16 | 66281 | 1144;1141 | 25642 | 3,7,11,13,17,21,29 | 260 |
| 17 | 69047 | 1100;1271 | 24308;27186 | 2,7,10,13,17,18,20,27 | 534 |
| Total | | | | | **6,041** |

61. በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን በፕሮጀክት ያሉ መሳሪያዎች አንድ አይነት የነዳጅ ፍጆታ፣ የስራ ጫና እና የስራ ሰዓት ኖሯቸው ሰፊ የነዳጅ አጠቃቀም ልዩነት ያላቸው እንዲሁም ትንሽ ሰዓት የሰሩ መሳሪያዎች ብዙ ከሰሩት የነዳጅ ፍጆታቸው የሚበልጥ መሆኑን ከተከለሱ ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. በተጨማሪም በ2009 ህዳር ወር ላይ መገጭ ግድብ ፕሮጀክት ላይ ተሽከርካሪዎች (ታርጋ ቁጥር፡- 3-28741፣ 3-47223፣ 3-78119፣ 3-78120፣ 3-28895፣ 3-58108፣ 3-30157፣ 3-62554፣ 3-24056፣ 3-26952፣ 3-68770፣ 3-73057 ) የሰሩበት ሰዓት ሳይኖር 4,722 ሊትር ናፍጣ እንዲሁም ማሽነሪዎች (መለያ ቁጥር፡- 3334፣ 031467፣ 1635፣ 21023፣ 18745) የሰሩበት ሰዓት ሳይኖር 5,888 ሊትር

ናፍጣ በአማካይ ብር 88,320 ነዳጅ የተጠቀሙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

63. በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን በቀድሞው የአርዳይታ ምርጥ ዘር እርሻ ልማት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለእርሻ መሳሪያዎች በመስክ ላይ በቦቴ ነዳጅ በሚታደልበት ወቅት ቦቴው ነዳጅ መቅጃ ቆጣሪ (counter) የሌለው በመሆኑ የሚቀዳው የነዳጅ መጠን ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ እና የማይመዘገብ መሆኑ ታውቆ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

64. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ኮንስትራክሽን የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ችግሩ በየወሩ የሚከሰት በመሆኑና ከስራ መዳደራረብ፣ የድርጅቱ የስራ ባህሪ የፈጠረው ጫና በመሆኑ የታዩትን ችግሮች ለወደፊት ለማስተካከል ጥረት እንደሚደረግ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

65. በኢትዮጲያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ዘርፍ የበላይ ሃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ማሽነሪዎቹ የሰሩበት ሰዓትና የነዳጅ ፍጆታቸው ልዩነት ያመጣው የስራ ጫና ስላለባቸው ነው፤ ነገር ግን መግለጫ ማዘጋጀት ነበረብን ያሉ ሲሆን የስራ ሰዓት ሳይኖራቸው ነዳጅ የተጠቀሙ ግን ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል፡፡

66. በኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን በቀድሞው የአርዳይታ ምርጥ ዘር እርሻ ልማት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው ስለጉዳዩ ለዋናው መስሪያ ቤት ያሳወቁ መሆኑና ችግሩን ለመፍታት ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

67. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው ሚ/ር መ/ቤቱ ከተቋቋመ የአንድ አመት ቆይታ ያለው ስለሆነ ችግሮችን በመለየት እርምጃ መውሰድ አለመጀመሩን እና በቀጣይ እንዲያስተካክሉ ሰርኩላር እንዲተላለፍ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

68. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን አለመዘርጋት ተጠያቂነት እንዳይኖር በማድረግ ነዳጅ ለታለመለት ተግባር እንዳይውል እና በውድ ዋጋ የሚገኘውን ነዳጅ ለምዝበራ እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

**የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ላይ ስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፡-**

69. የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የስምሪት ባለሙያዎች ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

70. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት ሁሉም የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ቁጥጥር፣ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ለስምሪት ባለሙያዎችና ለነዳጅ አዳዮች ስልጠና እንዲያገኙ እና ግንዛቤ እንዲጨብጡ አለመደረጉ፣ በተሽከርካሪ ስምሪት ላይ የሚመደቡ ባለሙያዎች በነዳጅ አጠቃቀም ቁጥጥር ላይ ያላቸውን ዕውቀት እንዲያሻሽሉ እና ከአዳዲስ የአሰራር ዘዴዎች ጋር እንዲተዋወቁ የሚረዳ ስልጠና ያልወሰዱ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

71. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ለነዳጅ አዳዮች ስለ ነዳጅ ጥራት በተመለከተ ስልጠና የተሰጠ ቢሆንም ለስምሪት ባለሙያዎች እና ለነዳጅ አዳዮች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ስልጠና አለመሰጠቱን ገልጸዋል፡፡

72. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡ በነባራዊ ሁኔታ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ተጠይቀው ይህን አሰራር ያላከናወኑትን በመለየት ለወደፊት እንዲያስተካክሉ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

73. የነዳጅ አጠቃቀምን እና አስተዳደርን በተመለከተ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ስልጠና በመስጠት በየጊዜው አሰራራቸውን እንዲያሻሽሉ ሥራውን በሥልጠና አለመደገፍ በሥራው የሰለጠነ እና ልምድ ያለው ባለሙያ እንዳይኖር ሊያደርግ እና በነዳጅ አጠቃቀም ወቅት የሚሞሉ ቅጾችና ትንተናዎች ወቅታዊ እና ወጥ እንዳይሆኑ በማድረግ ለአሠራር እና ለቁጥጥር አመቺ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓት እንዳይኖር በማድረግ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ተገዝቶ የሚመጣውን ነዳጅ አለአግባብ ለመጠቀም በር ሊከፍት ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

75. በመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የመንግስት ልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር በቁጠባ፤ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ግድፈቶችና ጉድለቶች ተገኝተዋል፡፡

- የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ዕቅድ ሲታቀድ የተሽከርካሪዎቹንና ማሽነሪዎችን ብዛት፤ ዓይነትና የነዳጅ ፍጆታን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ እና መካተት ያለባቸው መነሻዎችን ሳያገናዝብ በጥቅል የሚታቀድ መሆኑ፣
- የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚ/ር ወጥ /Standardized/ የሆነ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፤ የነዳጅ አጠቃቀም፤ የቁጥጥር እና አስተዳደርን አስመልክቶ መመሪያ ያላዘጋጀና የልማት ድርጅቶቹ እራሳቸው እንዲዘጋጁና ስራ ላይ እንዲያውሉ ያልተደረገ እና ጥናትም ያልተካሄደ መሆኑ፣
- በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ዲፖ አስተዳደር የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋና መመሪያ የሌላቸው መሆኑ፤ የነዳጅ ማደያ ዲፖዎች ለረጅም ጊዜ እድሳት ያልተደረገላቸው መሆኑ ፣ የነዳጅ መቅጃ መሳሪያዎቹ በትክክል አገልግሎት የሚሰጡ ስለመሆኑ (calibration test) በየወቅቱ አለመደረጉ፣ የነዳጅ መቅጃ የመጠን መቁጠሪያቸው (counter) የማይሰራ ዴፖዎች መኖር፣ የነዳጅ ማደያ ዲፖዎቹ የእሳት አደጋ መከላከያ (Fire extinguisher) አለመኖር፤
- የልማት ድርጅቶቹ ወጥ በሆነና ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ የነዳጅ፣ የዘይት እና የቅባት መመዝገቢያ ቅጽ አዘጋጅተው ተግባራዊ ያላደረጉ መሆኑ፣
- የእያንዳንዱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን ተመዝግቦ የማይታወቅና ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ የነዳጅ ጥያቄ ማቅረብ ያለባቸው የተሞላው ነዳጅ ምን ያህል ሲቀረው መሆን እንዳለበት የሚያደርግ መስፈርት /Standard/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

- እያንዳንዱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪሎ ሜትር መጓዝ እንደሚችሉ መስፈርት ያልወጣላቸው መሆኑ፤
- የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ፍጆታ ኮታ ያልወጣላቸው መሆኑ፣
- አገልግሎት የሰጡ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታቸው ስለሚጨምር የነዳጅ ኪሎ ሜትር አጠቃቀም በየዓመቱ ለቁጥጥር ተግባር በሚመች ሁኔታ ተለክቶ፣ ያልተረጋገጠ፣ ያልተመዘገበና ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የልማት ድርጅቶቹ እያንዳድንዱ አዳዲስ ተሽከርካሪዎች የሚጠቀምበትን ነዳጅና የሚጓዝበትን ኪሎ ሜትር ከአምራች ኩባንያው በሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የማይነጻጸር መሆኑ፤
- በመንግስት የልማት ድርጅቶች ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ካርድ (ሎግ ቡክ) የማይዘጋጅላቸውና የየዕለቱንና የየወቅቱን መረጃዎች ማለትም የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ፤ የሰርቪስ ከጥገና ወጪዎቻቸው ጋር ተነጻጽሮ የሚመዘገብበት የተሟላ የግል ማህደር አለመኖሩ፣
- የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ኪሎ ሜትር ቆጣሪው/ ጌጅ የሚሠራ ስለመሆኑ በየጊዜው የማይረጋገጥ እና ጌጃቸው ለማይሠሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋና በዛም መሠረት ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣
- በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ያልተዘረጋና በዚሁ መሠረት የግብረ መልስ አሰጣጥ ሥርዓት ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ሥራ ላይ ሳይሆኑ ሥራ እንደሰሩ እየተደረገ ነዳጅ የሚቀዳ መሆኑ፣

- የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የስምሪት ባለሙያዎች የስልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አለመከናወናቸው፣
- ስለሆነም ከላይ የተገለጹት አፈጻጸም ላይ የታዩትን ድክመቶችና ግድፈቶች በነዳጅ አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩ፤ በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓታቸውን ጠብቀው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

76. ሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ዕቅድ በጥናት ላይ በመመስረት ሊያዘጋጁ እና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚ/ር የልማት ድርጅቶቹ የሚጠቀሙበት ወጥ /Standardized/ የተሽከርካሪዎች ስምሪት፣ የነዳጅ አጠቃቀም፣ የቁጥጥር እና አስተዳደር መመሪያ ሊያዘጋጅ፣ መመሪያውም በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋና እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚ/ር መ/ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደርን አስመልክቶ ጥናት ሊያካሄድ እና በጥናቱ በተለዩ ችግሮች ላይ የመፍትሄ ሃሳብ ሊሰጥ ይገባል፡፡
- የነዳጅ ዲፖ ያላቸው የመንግስት የልማት ድርጅቶች ነዳጅ ሲገዛም ሆነ ወደ ዲፖ ሲገለበጡ ግልፅ የሆነ የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶቹ ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ የነዳጅ ጥያቄ ማቅረብ ያለባቸው የተሞላው ነዳጅ ምን ያህል ሲቀረው መሆን እንዳለበት የሚገልጽ መስፈርት /Standard/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የዘይት እና የቅባት መመዝገቢያ ቅጽ ሊዘጋጅላቸውና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የእያንዳንዱ የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን አስቀድሞ በማወቅ ተመዝግቦ ሊያዝ እና በዚሁ አግባብ ስለመሞላቱ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- እያንዳንዱ የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል እና እያንዳንዱ ማሽነሪ በሰዓት ምንያህል የነዳጅ መጠን እነደሚጠቀም መስፈርት ተዘጋጅቶና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ለአንድ ተሽከርካሪ ነዳጅ ከመሙላቱ በፊት በነዳጅ ማጠራቀሚያው ውስጥ ያለው ነዳጅ እና የተጠቀመው ነዳጅ ታውቆ ከተወሰነለት ኮታ ጋር የሄደበት ኪ.ሜ. ርቀት በማነጻጸር በተፈቀደለት ኮታ ብቻ ስለመጠቀሙ ሊረጋገጥና የነዳጅ ቅጽ ፈቃድ ሊሞላ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጄነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ኮታ አዘጋጅተው በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- ለእያንዳንዱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ካርድ (ሎግ ቡክ) በማዘጋጀት የየዕለቱንና የየወቅቱን መረጃዎች ማለትም የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ፣ የሰርቪስ ከጥገናና ወጪዎቻቸው ጋር የሚመዘገብበት የተሟላ የግል ማህደር ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ኪሎ ሜትር ቆጣሪው፣ ጌጅ የሚሠራ መሆኑ በየጊዜው መረጋገጥ አለበት፡፡
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጌጃቸው ለማይሠሩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋና በዚሁ መሠረት ሊተገበር ይገባል፡፡
- አገልግሎት የሰጡ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታቸው ስለሚጨምር የነዳጅ ኪሎ ሜትር አጠቃቀም በየዓመቱ ለቁጥጥር ተግባር በሚመች ሁኔታ ተለክቶና ተረጋግጦ ሊመዘገብ እና በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የልማት ድርጅቶቹ እንዳድንዱ ተሽከርካሪ የሚጠቀምበትን ነዳጅና የሚጓዝበትን ኪሎ ሜትር ከአምራች ኩባንያው ከሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሊነጻጸር እና ልዩነቱንም ከአስፈላጊው ማብራሪያ ጋር ሊገለጽ ይገባል፡፡
- በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የነዳጅ አጠቃቀምን አስመልክቶ የተከሰቱ ችግሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ በሚ/ር መ/ቤቱ ወይም በድርጅቶቹ የበላይ ኃላፊዎች ሊወሰድ ይገባል፡፡
- የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የስምሪት ባለሙያዎች ስልጠና እና ግንዛቤ በልማት ድርጅቶቹ ሊሰጥ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የልማት ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ 2. የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| የኦዲት ጭብጥ /Issues/ | የመገምገሚያ መስፈርት /Evaluative Criteria/ | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| 1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማደረጋቸውን እንዲሁም በጥናት ላይ የተመሰረተ የነዳጅ ፍላጎት ዕቅድ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት እየተገበሩ መሆኑን መገምገም፣ | 1.1 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚመሩበት ወጥ /Standardized/ የሆነ የነዳጅ አጠቃቀም መመሪያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ | |
| | 1.2 ሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደር ዕቅድ ሊያዘጋጁ ይገባል፡፡ | |
| | 1.3 በመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የተዘጋጀውን መመሪያ መሰረት በማድረግ መተግበሩንና መመሪያው በየጊዜው ወቅታዊ የሚደረግበት አሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 1.4 የልማት ድርጅቶች የነዳጅ ግዥና አስተደደር ሥርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ | |
| | 1.5 ሚ/ር መ/ቤቱ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም እና አስተዳደርን አስመልክቶ ጥናት ሊያካሂድ ይገባል፡፡ | |
| | 1.6 ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የተመደበው የነዳጅ በጀት አፈጻጸም መጣጣሙ በየሩብ ዓመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ | |
| | 1.7 የነዳጅ ዲፖ ያሉዋቸው የልማት ድርጅቶች ግልፅ የሆነ የዲፖ አስተዳደር የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| | 1.8 ተሽከርካሪዎች ተጨማሪ የነዳጅ ጥያቄ ማቅረብ ያለባቸው የተሞላው ነዳጅ ምን ያህል ሲቀረው መሆን እንዳለበት የሚያደርግ መስፈርት /Standard/ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 1.9 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች ፣ጄኔሬተሮች እና ማሽነሪዎች ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ነዳጅን እንዲጠቀሙ በየጊዜው የመደበኛ የጥገና (ሰርቪስ)ና የእንክብካቤ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 1.10 የአንድ ተሽከርካሪ ግዥ ጥያቄ ሲቀርብ የነዳጅ፣ ቅባት እና ጥገናው ወጪ ውጤታማነት አብሮ ሊታይ ይገባል፡፡ | |
| 2. በመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ በቁጠባ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተተገበረ መሆኑን ማጣራት፣ | 2.1 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዕለታዊ የነዳጅ፣ የነዳጅ፣ የዘይት እና የቅባት መመዝገቢያ ቅጽ /ሎግ ቡክ/ ሊዘጋጅላቸውና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 2.2 የእያንዳንዱ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ታንከር (ሰልባቲዮ) የሚይዘው የሊትር መጠን አስቀድሞ በማወቅ ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡ | |
| | 2.3 እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በዓይነትና በሞዴል ተለይተው በአንድ ሊትር ነዳጅ ስንት ኪ/ሜትር መጓዝ እንደሚችል መስፈርት /Normalization rate/ በገለልተኛ አካል ተዘጋጅቶና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 2.4 አንድ ተሽከርካሪ መጠቀም ያለበት ነዳጅ ከመሙላቱ በፊት በነዳጅ ማጠራቀሚያው በሚይዘው መጠን/በተወሰነለት ኮታ መሰረት | |

| | | |
|---|---|---|
| | የሄደበት ኪ.ሜ. ርቀት ሊረጋገጥና የነዳጅ ቅጽ ፈቃድ ሊሞላ ይገባል፡፡ | |
| | 2.5 ለኃላፊዎች ለሰርቪስ አገልግሎት የሚመደብ ተሽከርካሪ በወር ውስጥ ምን ያህል ሊትር ነዳጅ መጠቀም እንዳለባቸው የሚገልጽ መስፈርት ተዘጋጅቶና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 2.6 የልማት ድርጅቶች ለሚጠቀሙባቸው ጀነሬተር፣ የግንባታ ማሽነሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም ሥርዓትና የነዳጅ ኮታ (በሰዓት እያንዳንዱ ጀኔሬተርና ማሽነሪ የሚጠቀሙት ነዳጅ መጠን) ተዘጋጅቶ በዚሁ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 2.7 በመንግስት የልማት ድርጅቶች ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የህይወት ታሪክ መመዝገቢያ ካርድ (ሎግ ቡክ) በማዘጋጀት የየዕለቱንና የየወቅቱን መረጃዎች ማለትም የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ፣ የሰርቪስ ከጥገናና ወጪዎቻቸው ጋር የሚመዘገብበት የተሟላ የግል ማህደር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ | |
| | 2.8 የነዳጅ ኩፖን ተዘጋጅቶና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተፈርሞ በወቅቱ ለተፈቀደለት ተሽከርካሪ ብቻ ሊቀዳ ይገባል፡፡ | |
| | 2.9 ከየስራ ክፍሉ የሚቀርቡ የተሽከርካሪ ጥያቄ በተሽከርካሪ ዕለታዊ የመጠየቂያ ቅፅ ተሞልቶ በሚመለከተው አካል ፀድቆ ለስምሪት ቡድን ስምሪት ሊከናወን ይገባል፡፡ | |
| | 2.10 ነዳጅ በሚሞላበትና የነዳጅ ኩፖን በሚሰጥበት ወቅት የተሽከርካሪው የኪሎ ሜትር ንባብና የሚሞላው የነዳጅ መጠን | |

| | | |
|---|---|---|
| | በቅጽ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡ | |
| | 2.11 አሽከርካሪው በተሰጠው ኩፖን ነዳጅ ከሞላ በኃላ ከማደያው ህጋዊ ደረሰኝ በመውሰድ ሲቀዳ የነበረውን ኪሜ ንባብ በመመዝገብ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ሊያቀርብ ይገባል፡፡ | |
| | 2.12 የሰርቪስ ጥያቄ ያቀረቡ ሰራተኞች ሲመጡ የሞሉትን ቅጽ ተመልክቶ የሰርቪስ አገልግሎት መስጠትና አገልግሎት ሲጨርሱ ተሽከርካሪው የተመለሰበትን ሰዓት በቅጹ ላይ ማስፈር ይኖርባቸዋል፡፡ | |
| | 2.13 የእያንዳንዱ ተሽከርካሪው ኪ/ሜትር ቆጣሪው/ ጌጅ የሚሠራ መሆኑን በየጊዜው መረጋገጥ አለበት፡፡ | |
| | 2.14 ጌጃቸው ለማይሠሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አጠቃቀም እና ቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ | |
| | 2.15 አገልግሎት የሰጡ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታቸው ስለሚጨምር የነዳጅ ኪሎ ሚትር አጠቃቀም በየዓመቱ ለቁጥጥር ተግባር በሚመች ሁኔታ ተለክቶና ተረጋግጦ ሊመዘገብ ይገባል፡፡ | |
| | 2.16 የልማት ድርጅቶቹ እንዳድንዱ ተሽከርካሪ የሚጠቀምበትን ነዳጅና የሚጓዝበትን ኪሎ ሜትር ከአምራች ኩባንያው በሚሰጠው የአጠቃቀም መመሪያ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ሊነጻጸር እና ልዮነቱንም ከምክንያት ጋር ሊገለጽ ይገባል፡፡ | |
| | 2.17 ለስራ ክፍሎች በየቀኑ የሚሠጥ የተሽከርካሪ ስምሪት ዝርዝር ሪፖርት ለዚሁ በተዘጋጀው ቅፅ ተሞልቶ ለሚመለከተው ኃላፊ መቅረብ | |

| | | |
|---|---|---|
| | ይኖርበታል፡፡ | |
| | 2.18 በየወሩ መጨረሻ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን ነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜትር ብዛት ጋር በማነጻጸር በሪፖርት መልክ ተቀናብሮ በቅጽ ላይ በመሙላት ለሚመለከተው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የሚቀርብበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 2.19 ተሽከርካሪው (አሽከርካሪው) በተደጋጋሚ ከተቀመጠለት እስታንዳርድ ውጪ የሚጠቀም ከሆነ የተሽከርካሪው የነዳጅ አጠቃቀሙ በባለሙያ ሊፈተሽና በውጤቱ መሰረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ | |
| | 2.20 የመንግስት የልማት ድርጅቶች የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ | |
| | 2.21 የነዳጅ አጠቃቀምን አስመልክቶ የተከሰቱ ችግሮችን በመለየት የማስተካከያ እርምጃ በመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ሊወሰድ ይገባል፡፡ | |
| | 2.22 የነዳጅ አጠቃቀምና አስተዳደርን በተመለከተ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች የስምሪት ባለሙያዎች ስልጠና በመስሪያ ቤቱ ሊሰጥ ይገባል፡፡ | |
| | 2.23 የሁሉም የመንግስት የልማት ድርጅቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት ክፍል ተግባርና ኃላፊነታቸው በጽሑፍ በግልጽ ሊቀመጥና ለእያንዳንዳቸው ሊደርሳቸው ይገባል፡፡ | |

## አባሪ 3. የአሰራር ሥርዓቱ (Process Description)

## አባሪ 4፡ በወር ውስጥ ከተፈቀደው የነዳጅ ኮታ (200 ሊትር) በላይ የተቀዳ ነዳጅ

| ተ.ቁ | የሂሳብ ቁጥር | የተሽከርካሪው የጎን ቁጥር | የተፈቀደ ነዳጅ ኮታ በወር | የተቀዳ ነዳጅ | ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1060 | 00001 | 200 | 250 | 50 |
| 2 | 1126 | 01911 | 200 | 440 | 240 |
| 3 | 1201 | 03776 | 200 | 273 | 73 |
| 4 | 1126 | 04440 | 200 | 529 | 329 |
| 5 | 1126 | 23526 | 200 | 408 | 208 |
| 6 | 1250 | 33503 | 200 | 900 | 700 |
| 7 | 1250 | 34611 | 200 | 220 | 20 |
| 8 | 1030 | 42645 | 200 | 295 | 95 |
| 9 | 1126 | 42974 | 200 | 260 | 60 |
| 10 | 1062 | 44961 | 200 | 260 | 60 |
| 11 | 1126 | 47490 | 200 | 340 | 140 |
| 12 | 1122 | 48089 | 200 | 290 | 90 |
| 13 | 1272 | 48984 | 200 | 264 | 64 |
| 14 | 1250 | 50225 | 200 | 350 | 150 |
| 15 | 1132 | 50849 | 200 | 348 | 148 |
| 16 | 1051 | 55070 | 200 | 255 | 55 |
| 17 | 1126 | 59008 | 200 | 382 | 182 |
| 18 | 1126 | 59011 | 200 | 417 | 217 |
| 19 | 1126 | 59012 | 200 | 513 | 313 |
| 20 | 1080 | 62567 | 200 | 310 | 110 |
| 21 | 1212 | 65179 | 200 | 390 | 190 |
| 22 | 1141 | 66281 | 200 | 260 | 60 |
| 23 | 1271 | 69047 | 200 | 534 | 334 |
| 24 | 1142 | 69723 | 200 | 250 | 50 |
| 25 | 1131 | 72950 | 200 | 398 | 198 |
| 26 | 1070 | 76801 | 200 | 303 | 103 |
| 27 | 1201 | 85861 | 200 | 292 | 92 |
| 28 | 1021 | 85907 | 200 | 331 | 131 |
| 29 | 1262 | 92969 | 200 | 334 | 134 |
| 30 | 1273 | 31932 | 200 | 337 | 137 |
| | | | **ድምር** | **10,733** | **4,733** |